# የኢንዱስትሪው ዘርፍ የሁለት ዓመታት ስኬታማ ጉዞ

**በኃይሉ መላኩ**

ታላቁ መሪያችን ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የመነጨ በሂደትም ሀገራችንን ከድህነት የሚያላቅቅ ማስመር ከጓዶቻቸው ጋር ቀይሰው ለተግባራዊነቱም ሌት ተቀን ደክመዋል፡፡ በሁሉም ዘርፎች ሀገሪቱ ልታሳካቸው የሚገቡ ግቦችንም አስቀምጠዋል፡፡ ከእነዚህ በርካታ የልማት ዕቅዶች ውስጥ ደግሞ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ተጠቃሽ ነው፡፡

አብዛኛው የሀገራችን ህዝብ በከፋ ድህነት ውስጥ በነበረበት በደርግ ወድቀት ማግስት በፍጥነት ዕድገት ለማስመዝገብ ከዚህ የድህነት አረንቋ ለመውጣትና ትክክለኛውን ማስመር ለመከተል የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በሚገባ የተረዳ በሳል መሪ ጠንካራ ድርጅት ያስፈልግ ነበር፡፡

በመሆኑም ከ85 በመቶ በላይ ህዝቦቿ ገጠርን ማዕከል ባደረገ የግብርና ስራ የሚተዳደሩት በመሆናቸው መጻዒ ዕድሏን በጠንካራ መሰረት ላይ ለመጣል ግብርና መር የኢኮኖሚ ፖሊሲ መከተል ብቸኛው አማራጭ መሆኑን የመሪነቱን ኃላፊነት የተረከቡት ኃይሎች በሚገባ ማንዘባቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡

ታዲያ እነዚህ ሃይሎች ራዕያቸውን በግብርና ላይ ብቻ በማንጠልጠል ለዘላቂ ሀገራዊ ግንባታ ወሳኝ የሆነውን የኢንዱስትሪ ዘርፍ የዘነጋ አልነበረም፡፡ ይልቁንም የዘርፉን ተመጋጋቢነት በመፍጠር ግብርናው የራሱን ወሳኝ ድርሻ ከተወጣ በኋላ የመሪነት ሚናውን ለኢንዱስትሪው የሚያስረክብበት ሁኔታ ለማመቻቸት ያለመ ነው፡፡

በኢንዱስትሪው ዘርፍ የጠቅላይ ሚኒስትራችንና ድርጅታቸው የረጅም ጊዜ ዕቅድ የአርሶ አደሩን የካፒታል አቅም በማሳደግ የማኑፋክቸሪንግ ጥሬ ዕቃዎችን በብዛትና በጥራት በማምረት ቀስ በቀስ ወደ ኢንዱስትሪው ማሸጋገር እንዲችል ማድረግ ነው። በዚህም የገጠር ወጣቶችን የዕድሉ ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲሁም ሴቶች በቤት ውስጥ የሚከሩትን ቀላል ስራዎችን በሂደት በፋብሪካ በመተካት ጭሱ በጭሱ ከቤት ውስጥ የኑሮ ጫና ለማላቀቅ ያለመ አቅጣጫ ነበር፡፡

በከተማው ደግሞ በአነስተኛና ጥቃቅን ስራ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ ስራ አጥነትን በመቅረፍ በሂደት የሚፈጠሩ የስራ ዕድሎች ወደ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችን የሚያድጉበትን አቅጣጫ ቀይሷል፡፡

መንግስት በነደፈው አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማትን የማስፋፋትና የመደገፍ ስትራቴጂ መሠረት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን ወደ ባለሃብትነት ወይም ወደ መካከለኛ ኢንዱስሪ ተሸጋግረዋል፡፡

በዚህ ተግባር ባለፈው ዓመት 250 ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ ባለሃብትነት /መካከለኛ ኢንዱስትሪ/ መሸጋገራቸው የሚታወስ ነው፡፡ ይህ ተግባር የሚያመለከተው መንግስት ዘርፉን ለማሳደግ የቀረፀው ፖሊሲና ስትራቴጂ ውጤታማ መሆኑን ነው፡፡

ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ ከተሸጋገሩት ወስጥም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ዜጎች በኮንስትራክሽን ዘርፍ በማሰማራት ላይ ይገኛሉ፡፡ ለአብነት ያህል የአዲስ አበባ ከተማን እንኳን ብንመለከት በ27 ማህበራት የተደራጁ ስድስት የስራ ተቋራጮች ሰርተፍኬትና እውቅና ተሰጥቷቸዋል፡፡

እነዚህ ማህበራት መንግስት ያስቀመጠውን አቅጣጫ ተከትለው ለስኬት የበቁ ናቸው፡፡ ይህ ዕውነታም በአነስተኛ ጥቃቅን ተቋማት ዘርፍ የተገኘው ውጤት በሌሎች ግዙፍ ኢንዱስትሪዎችም እየተደገመ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በተግባር እንደታየውም የሀገራችን አርሶ አደር ሜቱንና ጉልበቱን በማጠቀም በታሪካችን ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ሚሊየነር መሆን ጀምሯል፡፡

በዚያው ልክም በኢንዱስትሪው ዘርፍ ሰፊ የሰው ጉልበት በማጠቀም ሀገራችንን ከውጭ ጥገኝነት ማላቀቅ ጀምሯል፡፡ በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ማብረት ትግበራ የሁለት ዓመታት ትግበራ ውጤት የሚያሳየው ይህንንኑ ነው፡፡

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ባለፉት 21 ዓመታት ግብርና መር ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲ ከድህነት ጋር ስተተናነቅ ቆይታለች፡፡ ውጤታማም ሆናበታለች፡፡ በተለይ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት በዓለም አቀፍ ደረጃ

በአብነት የሚጠቀስ ዕድገት ማስመዝገብ ችላለች፡፡ የአርሶ አደሩ ኑሮም ከመሻሻል አልፎ ከፒታል ማፍራት ጀምሯል፡፡

በአሁኑ ወቅት ጥቂት የሚይባሉ አቅማቸው የጎለበቱ የህብረት ስራ ማህብራት ወደ ኢንዱስትሪው እየተሸጋገሩ ነው፡፡ በዚህም የዱቄት፣ የማዳበሪያ፣ የቡና ሚፈልፈያ፣ የምግብ ማቀነባበሪያ፣ ዘመናዊ የማር ምርት የሚያቀርቡ እና ማሳል ፋብሪካዎችን እየገነቡ ይገኛሉ፡፡ ይህም ግብርናው ለኢንዱስትሪ ሐብት እየፈጠረ ማሆኑን ዋነኛ ማሳያ ነው፡፡

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የሁለት ዓመታት ወስጥ መንግስት ኢንዱስትሪወን ለማሳደግ በርካታ ጥረቶችን አድርጓል፡፡ ጥቂቱን ለመጥቀስ ያህል የሀገር ወስጥና የውጭ ባለሀብቶችን አወያይቷል፡፡ በህብረተሰቡ ወስጥ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ሰርቷል፡፡

ከዘህ ባሻገርም የዘርፉን ተዋንያን ለማበረታታት ሽልማት እየሰጠ ጀምር እንቅስቃሴዎችን አበረታትቷል፡፡ ወጤታማ የሆኑት ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሸጋገሩ የሚያግዙ ተግባራትን ሁሉ አከናወኗል፡፡ በዚህ ምቹ ሁኔታ በማጠቀምም በርካታ የወስጥና የውጭ ባለሀብቶች በዘርፉ በብዛት ኢንቨስት በሚድረግ ላይ ናቸው፡፡

ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ ቆዳና የቆዳ ወጤቶች፣ የአግሮ ኘሮሰሲንግ ምርቶችና የፋርማሲካልና የኬሚካል ወጤቶች ድምር ዕድገት በ2004 ዓ.ም ካለፋት ጊዜያት ጋር ሲነፃፀር ከ22 በመቶ በላይ እድገት አሳይቷል። ይህም ዕቅዱ በትክክለኛ ማስመር ላይ እየተጓዘ ማሆኑን አብይ ማሳያ ነው፡፡

ለዚህ ዘርፍ እንደተቀሩት የኢንዱስትሪ ዘርፎች ሁሉ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞችን ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ማስተሳሰር ተችሏል፡፡ የሚፈለገወን የሰው ሃይል በአስተማማኝ ለማልማት ከቴክኒክና ሙያ እንዲሁም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር የማቀራረኘት ስራ በሚደበኛ፣ በረጅምና በአጫጭር ስልጠናዎች የዘርፋ አቅም የማንባት ስራ ተከናወኖ ወጤት ተገኝቶባቸዋል፡፡

በመሆኑም እስከ አሁን ለታየው ዕድገት በምክንያትነት የሚጠቀሱትን ለባለሙያዎች የሙያ ማሻሻያ ስልጠና እንዲሁም የተቀላጠፈ የፋይናንስ፣ የጉምሩክና የሎጀስትቲክ አገልግሎት ድጋፍ ማስጠትና አስፈላጊ ማሻዋወጫዎችን በሀገር ወስጥ ማምረት ቀጣይ ትኩረት የተሰጣቸው የሁለት ዓመት ስኬቶች ናቸው፡፡

ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮ የመውሰድ እና የቁርኝት ኘሮግራሞችን፣ ለፋብሪካ የሚያስፈልጉ ማሻዋወጫዎችን በሀገር ወስጥ የማምረት ጥረቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የተገኘወን ውጤት በማቀብ ዕድገቱን የበለጠ ለማጉጠንም በዘርፉ እቅድ ተይዟል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በኢንቨስትመንት ሂደት ላይ የሚገኙ ኘሮጀክቶች በወቅቱ ግንባታቸወን ተጠናቆ ወደ ምርት እንዲሸጋገሩ ክትትልና ድጋፍ የሚድረግ ስራም ቀጥሏል፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታት አዳዲስ ባለሃብቶችን ለማሳብ በኢንዱስትሪው ንዑስ ዘርፍ የኘሮጀክትና የአዋጭነት ጥናቶች ተደርጓል፡፡በተለያዩ መንገዶች ባለሃብቶችን ማስተዋወቅን ጨምሮ አዳዲስ የሀገር ወስጡና የውጭ ሀገር ባለሃብቶች በዘርፋ እንዲሰማሩ መደረጉ ስራው ተጠናክሮ እንዲቀጥል የበኩሉን አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡

በሂደት ላይ የሚገኙትን የኢንዱስትሪ ዞን የሚቋቋም ስራዎች ወደ ተግባር ለማሸጋገር የድጋፍና ክትትል ስራዎች በዝርዝር ተለይተው ተግባራዊ ውጤት አምጥተዋል፡፡

ኢንዱስትሪዎቻችንን በዓለም ገበያ የበለጠ ተወዳዳሪ ለሚድረግ በግብአትና በምርት ትስስር በገበያ ፍለጋ በሎጀስቲክ አቅርቦት፣ በፋይናንስና ብድር አቅርቦት፣ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ማስጠት በጥሬ አቅርቦትና ግብይት ስርዓት ላይ ያሉ ችግሮችን ከማስረቱ ለመፍታት ጥሬ ዕቃዎችን ከውጭ ማስገባትን ጨምሮ ሌሎችን ችግሮችን በዘላቂነት መፍታት ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች ሆነዋል፡፡

በዚሁ መሠረት በጨርቃጨርቅ፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ በአግሮኘሮሰሲንግ፣ በኬምካልና ፋርማሲዩቲካል ዘርፍ የተገኘው ውጤት በ2005 ዓ.ም ይገኛል ተብሎ ከሚገመተው የ112 ነጥብ ሦስት በመቶ ብልጫ እድገት ለማስመዝገብ ግብ ተጥሏል፡፡

በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በኢንዱስትሪው ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች ወስጥ የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ለአብነት ያህል በ2004 ዓ.ም ከቆዳው ውጤቶች ብቻ 100 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡ በበጀት ዓመቱ ከተቀመጠው ዕቅድ አንጻር የተሻለ አፈጻጸም እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታት በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍም ውጤታማ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ ከውጭ ሀገራት በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ይገቡ የነበሩ መለዋወጫ ማሽነሪዎች በሀገር ውስጥ መመረት ጀምረዋል፡፡ በተለይም የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ለኢንዱስትሪው ሽግግር ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡

እነዚህ ተግባራትም ጠቅላይ ሚኒስትራችን የኢንዱስትሪው ዘርፍ የፈጠሩ፣ ለዕድገቱ ዋነኛ አንቀሳቃሽ ሞተር የሆነና በሂደትም ከግብርናው የመሪነት ሚናውን እንዲረከብ ያስቀመጡት አቅጣጫ ፍሬያማ መሆን መጀመሩን ያመለክታል፡፡

ታላቁ መሪያችን በአመራር በቆዩበት ዓመታት ለኢንዱስትሪው ዘርፍ ዕድገት ማነቆ የሆኑትን ጉዳዮች በመለየት፣ ያለውን የአቅም ውስንነት፣ የምርት ጥራት ምርታማነት ዝቅተኛ መሆን እንዲሁም የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖር፣ የግብዓት አቅርቦት፣ የፋይናንስ ችግርና የድርጅታዊ አሰራር ችግሮችን በዝርዝር በመፈተሸ መፍትሄ የሆኑ በሳል አቅጣጫዎችን በማስቀመጣቸው ውጤቱ መታየት ጀምረዋል፡፡

ይሁንና ችግሮቹን ዘላቂ በሆነ መልኩ ለመፍታት ባለፉት ሁለት የዕድገት ዓመታት ዘርፈ ብዙ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ መንግስት በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዓመታት የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት አጠቃላይ ኢንዱስትሪውን የሚደገፍ ስራዎችን ገቢራዊ አድርጓል፡፡

እርግጥ ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ የበለፀገች ሀገር እንድትሆን ከተፈለገ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ በምርጥ ዘርና ማዳበሪያ አቅርቦት ራስን መቻል የግድ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡ እስካሁን ባለው ሂደት ለግብርና ግብአት የሆነውን ዩሪያና ዳፕ ማዳበሪያዎችን ከውጭ ሀገር እየገዛን እናስገባለን፡፡

ለአብነት ያህልም ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሜጨሻ ድረስ ከአንድ ሚልዮን ቶን የሚልቅ ማዳበሪያ ያስፈልገናል። ፍላጉቱ ደግሞ እያደገ የሚሄድ ነው፡፡ ለዚህን ያህል ማዳበሪያ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ስናስብ ደግሞ መፍትሔ መሻት የግድ ይላል፡፡

መንግስትም ለማዳበሪያ ግዢ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ለማስቀረት የማዳበሪያ ፋብሪካ ማንባት አማራጭ የሌለው መፍትሔ መሆኑን ከግምት ወስጥ በማስገባት እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡

በዚህ መሠረት በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ባለቤትነት አምስት የዩሪያና ሦስት የዳፕ ማዳበሪያ ፋብሪካዎች ግንባታ በኦሮሚያ ክልል ተጀምሯል፡፡ ግንባታውን የሚያከናውነው የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን መሆኑ ደግሞ የውጭ ምንዛሬን በማስቀረት ረገድ የሚኖረው አስተዋፅኦ ሳይታለም የተፈታ ጉዳት ነው-"የሀገሩን በሬ በሀገሩ ሰርዶ" እንዲል የሀገራችን ሰው።

ፋብሪካዎቹ ግንባታቸው ተጠናቆ በሙሉ አቅማቸው ማምረት ሲጀምሩ የአርሶ አደሩን የግብአት አቅርቦት ችግር በመቅረፍ ለዚሁ ግዢ ይወጣ የነበረውን የውጭ ምንዛሪ ለማስቀረትና ለዜጎች የስራ እድል በመፍጠር ረገድ የሚኖራቸው ሚና ይጫወታሉ፡፡

በኢንዱስትሪ የበለፀገች ኢትዮጵያን ለመፍጠርም መደላደል ይፈጥራሉ፡፡ በሂደት ደግሞ አቅምን አጉልብቶ ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሪ ገቢን ለማስገኘት የሚቻልበትን እድል መፍጠራቸው አይቀሬ ነው፡፡

በዚህ መስረት የኢንዱስትሪ ዞኖች ተለይተዋል፡፡ በዞኖቹ መስረተ ልማቶችን አሟቷ በሆነ መልኩ ለማሟላት ጥረት ተደርጓል፤እየተደረገም ነው፡፡ ከዚህ መነ ለመነም በኢንዱስትሪው መስክ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች የሚያመርቱት ምርቶች ጥራታቸው የጠበቁ እንዲሆኑ በብዛት ማምረት እንዲችሉ ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑም ጥረቱ ቀጥሏል፡፡

በዚህ ዘመን በዓለም ገበያ ተወዳድሮ ማሸነፍና ጥራት ያለውን ምርት ማምረት የግድ ይላል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ "በዘመነ ግሎባላይዜሽን ለመቆም መሮጥ ያስፈልጋል፡፡ ለአፍታም ቢሆን መዝናናትና ማንቀላፋት የሚፈቅድ ስርዓት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ከፊት የነበሩ ሀገሮች ወደ ኋላ እየተመለሱ ነው" ማለታቸው ይታወሳል።

በአንጻሩ ከኋላ የነበሩ ሀገሮች ወደ ፊት በማስገስ ላይ እንደሚገኙና በዚህ የሽግግር ጊዜ ድርሻን ማሻሻል ከተፈለገ 24 ሰዓት በተጠንቀቅ መቆምን፣ በወድድር ማሸነፍን ሌት ተቀን የመወዳደር አቅምን ማሻሻል እንደሚጠይቅም በሚያሻማ ሁኔታ ገልፀው ነበር፡፡

እናም የታላቁ ሜያችንን በኢንዱስትሪ የበለጸገች ኢትዮጵያን የመፍጠር ራዕይ ለማሳካት ከመቼውም ጊዜ በላይ ጠንክሮ ማስራት የሚያስፈልግበት ወቅት ላይ እንገኛለን፡፡ በመሆኑም በዓለማችን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር የግል ባለሀብቱ የተወዳዳሪነት አቅሙን መሻሻል ይጠብቅበታል፡፡

ባለሃብቱን ለመደገፍም መንግስትም ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን የተሟ የሰው ኃይል ማፍራት ስራውን በስፋት ቀጥለበታል፡፡ በሜካም አስተዳደር በኩልም የሚያጋጥሙ ችግሮችን የሚያቃልሉ ርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡

በኢንዱስትሪው ማስክ የተሰማሩ ባለሀብቶች መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ጉልህ ስፍራ አላቸው። ባለሃብቶቹም ይህንኑ ከግምት ወስጥ በማስገባት የመንግስትን ጥሪ ተቀብለው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ናቸው፡ ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የሚደረገው ሽግግርም በመንግስትና በእነርሱ የላቀ ተሳትፎ በትክክለኛው ማስመር እየተጓዘ ነው፡

ነገ በምናያት በኢንዱስትሪ የበለፀገች ኢትዮጵያ ወስጥ ግንባር ቀደም ተዋናይ መሆናቸው ከአሁኑ በመታየት ላይ የሚገኘው በሺዎች የሚቆጠሩ የከተማ ነዋሪዎች በዘርፉ ተሰማርተው የተሳካና ወጤታማ ስራ በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

በያዝነው የአምስት ዓመት ዕቅድ ማጠናቀቅ በኋላ ከግብርና ሜ ወደ ኢንዱስትሪ ወደ ህብረተሰብ እንድትሸጋገር የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠር መንግስትና በግሉ ሴክተር የሚከናወኑ የኢንዱስትሪ ልማት ፕሮጀክቶችን ሲያስፋፋ ቆይቷል፡፡

በመሆኑም የግሉ ሴክተር ከሚያደርጋቸው ትላልቅ ልማታዊ ስምሪቶች ጎን ለጎን በማግስት ልማት ድርጅቶች የተለያዩ የኢንዱስትሪ ልማት ፕሮጀክቶች እንዲከናወኑ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከነዚህ መካከል ስራቸው ተጀምሮ በመፋጠን ላይ ያሉት አስር የስኳርና አንድ የማዳበሪያ ማምረቻ ፋብሪካ ይገኙበታል፡፡

ማግስት በተለይ የስኳር ፋብሪካዎችን በሀገራችን አቅም የማስራት ልምድ እንድናዳብርና ፋብሪካዎችን የማንባት አገራዊ አቅም እንዲኖረን በማሰብ በሚያካሂደው ልማት ሁሉም ስራዎች በተቀማጠለቸው አቅጣጫ እየተፈፀሙ ይገኛሉ፡፡

በመሆኑም ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገው ጉዞ በትክክለኛ ማንገድ ላይ ይገኛል ለማለት ያስደፍራል፡፡ እናም ሜጨው ጊዜ የኢንዱስትሪ ዘምን ማሆኑን የሚያመላክቱ ተግባራት ባለፉት ሁለት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ተፈፃሚ ማሆናቸው ህዳሴያችንን ቅርብ ማሆኑን አመላካች ናቸው ። የዚያ ሰው ይበለን።